# ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት. ዴ. ፓ)
# Tigray Democratic Party (T.D.P)

## <u>ለህወሓት አስቸኳይ ድርጅታዊ ጉባኤ የአቋም መግለጫ ከትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የተሰጠ ምላሽ</u>

የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ በድርጅቱ ታሪክ የመጀመሪያ ነው የተባለ አስቸኳይ ጉባኤ ከታሕሳስ 25 እስከ 26፣ 2012 ዓ/ም ያካሄደ ሲሆን ይኽንን በተመለከተም ያወጣውን መግለጫ ፓርቲያችን ተመልክቶት የሚከተለውን መግለጫ ማውጣት ግድ ብሎናል።

በመሰረቱ "አስቸኳይ ጉባኤ" ተብሎ የተጠራው ጉባኤ በተከታታይ ከተካሄዱት ቀደምት ሁለት ስብሰባዎች የተለየ ነገር ያልታየበትና በይዘትም የህወሃት ቁንጮዎች የተለመደና ተመሳሳይ የውሸት፣ የማስፈራራት እና የማወከብ ባህሪያቸውን የተንፀባረቀበት ጉባኤ ነው። ይኸም የማደናገር ስብሰባቸው በሚመለከት እውነታው ምን እንደሆነና እንደምታው ምንድነው የሚለውን ለትግራይ ህዝብ ብሎም ለኢትዮጵያ ህዝብ  ማሳወቅ የግድ ይላል።

በመሰረቱ ብዙ አቧራ እያነሱበት ያለውን የውህደት ጉዳይ ስንመለከት እነሱ ራሳቸው ይዘውሩት በነበረው የያኔው ኢህአዴግ ከአስር ዓመታት በፊት ጀምሮ ውህደቱ የሚያሳልጥ ሂደት ተጀምሮ በዚህ ዘርፍ የበቁ ምሁራንና ፖለቲከኞች ያሉበትን የአጥኚ ቡድን አቋቁመው ሂደቱን ጠብቆ ሲካሄድ መቆየቱ እና ጥናቱም መጠናቀቁ ልብ ይሏል። የህወሓት መሪዎች በባህዳሩ የኢህአዴግ ጉባኤም ሆነ በሌሎች አጋጣሚዎች ውህደቱ ዘግይቷል የሚል እሮሮአቸውን ሲያሰሙ ታሪክ መዝግቦታል። ታድያ ጥናቱ እነሱ በቀየሱት መንገድ እና ህጉን ጠብቆ ተጠናቆ ሲያበቃ ለውህደት ሲጠሩ ለምን ተቃዋሚ ሁነው ቀረቡ? በኢትዮጵያ ህዝቦች እና በኢህአዴግ ውስጥ በተፈጠረው የለውጥ እና የአልገዛም ባይነት አመፅ የማእከላዊ መንግስት ስልጣናቸውን ሲያጡ ውህደቱን መቃውም ጀመሩ። በመሆኑም የህወሓት መሪዎች የሚያነሱት የመርህና የአሰራር ጉዳይ ሳይሆን ላለፉት 27 ዓመታት ያላገጡበትንና የጨፈሩበትን የማዕከላዊ መንግስት ስልጣን ማጣታቸው የፈጠረው ስሜት እንጂ የህወሓት አመራሮች የፓርቲ ሕገደንብ እንኳን የማይገዛቸው ዋልጌዎች መሆናቸው የ1993 ዓ/ም 12ቱ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላትን ያባረሩበት ሕገወጥ ሂደት ማስታወስ በቂ ነው። የህወሓት አመራሮች ያለፈ የመንግስትነትም ይሁን የፓርቲ ታሪካቸውን በደንብ ለሚያውቀው የኢትዮጵያ ህዝብ የነሱን ፀረ-ዲሞክራሲያዊ እና አምባገነንነት ባህሪይ መንገር ለቀባሪው ማርዳት ይሆንብናል።

በመግለጫቸው የህግ ጥሰት እንዳጋጠመ፣ ጥገኛ ፓርቲ እንደተመሰረተና በህዝብ ላይ ክህደት እንደተፈፀመበት የገለፁ ሲሆን ነገር ግን ጥገኝነቱ በምን መልኩና ማን ላይ እንደሆነ፣ በምን መልኩ ሕጉ እንደተጣሰና  እና ክህደቱ እንደተፈጸመ ሳያብራሩት አልፈዋል። እንዲሁም ወረድ ብሎም በስም ያልጠቀስዋቸው የውጭ ሃይሎችን ያስጠነቀቁበትና የአፍሪካ መንግስታትና የአፍሪካ ህብረት የውጭ ጣልቃ ገብነትን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ጥሪ ያደረጉበት ጉዳይ ስንመለከት የህወሓት አመራሮች ምን ያህል ፍርሃትና ጭንቀት ላይ መሆናቸውን የሚያመለክት መግለጫ ነው። ይኸም በተካነው የሴራ አባዜ ታክቲካቸው ህዝቦችን ለማነሳሳትና አገር ኣበጣብጦ ወደ ነበሩበት ስልጣን ለመመለስ የታሰበ ተራ ሽፍጥ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው።

ሌላው ሊሰመርበት የሚገባው ነጥብ የትግራይ ህዝብንና ህወሓት አንድ ናቸው የሚለው ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል የሚለው ብሂል ተከትለው የሚነዙት መሰረተ-ቢስ ፕሮፖጋንዳ ነው። ለመሆኑ ህወሓት የማነው? ለምንስ ነበር የትግራይ ጀግና ልጆቹ መስዋእት የከፈሉለት?  ዓላማው ለምን ነበር? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ የነዚህ ጥቂት ከሀዲ የህወሓት መሪዎችን መሰሪ ዕላማ ለማጋለጥ ይጠቅማል። ደማቁ የህወሓት ፈታኝ ትግል የትግራይ ህዝብና ልጆቹ ትግል ነው። ታድያ ይኸ ከትግራይ አልፎ በመላ

ስልክ ቁጥር +251-118-65-13-36/+251-914-73-35-39/+251-940-79-08-22
Website: tigraydemocraticparty.com, email:tigraydemocraticparty@gmail.com
የካ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 13፣ ኣያት ጌት ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቤ.ቁ. 519፣ አዲስ አበባ፣
ገብረየሱስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቤ.ቁ. 59፣ መቐለ

ኢትዮጵያ ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ ጋር በመተባበር ደማቅ ታሪክ የተፃፈበት ተጋድሎ ከ1983 ዓ/ም ጀምሮ በጥቂት የህወሓት አመራሮች ፀረ-ህገመንግስታዊና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ባህሪይ ምክንያት መቀመቅ ከተውታል። ቅጥ ያጣው ሙስናቸውንና አምባገነንነታቸውን ለመሸፋፈን አሁንም በጭቁኑ የትግራይ ህዝብ ይነግዳሉ። ህዝቡንም በድህነት ወለል በመሸማቀቅ እንዲኖር እያደረጉት ነው። ለዚህም የትግራይ ህዝብ ልጆቹ የተሰዉለትን የህገመንግስቱን መብቱን ተጠቅሞ እነዚህን ከሀዲና በስሙ የሚነግዱትን ጥቂት የህወሓት አመራሮችን በቃቹ ሊላቸው ይገባል።

የህወሓት መሪዎች ምንም የዴሞክራሲና የስነምግባር ሽታ የሌላቸው መሆኑን የምንመለከተው ደግሞ በዚህ መግለጫ የሚያወርዱት የስድብና የማስፈራራት ውርጅብኝን ስናይ ነው። እነሱ ከፈለፈልዋቸው ፓርቲ ተብዬ ውጭ፣ ራሳቸውን የቻሉ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ላይ በትግራይ ክልል እንዳይንቀሳቀሱ ከፍተኛ የዛቻ፣ የማስፈራራት እና የማደናገር ዘመቻ ከመቼውም በባሰ ሁኔታ ከፍተውባቸዋል። አስነዋሪ ስሞችን በመስጠት ማለትም “ባንዳዎች፣ እንክርዳዶች፣ ነጋዴዎች” የሚሉ የዘቀጡ አባባሎች በመጠቀም ራሳቸውን ማቅለላቸው መገንዘብ ይቻላል። ይህ ብቻ አይደለም! ለረጅም ዓመታት አብሮአቸው ውህደት ሲፈጥሩ የነበሩት ሶስቱ (የኦሮሞ፣ የአማራና የደቡብ ህብረት) ድርጅቶች እንደ ከሃዲዎች፣ ህገወጥና ጥገኛ ፓርቲዎች በመቁጠር ሃገር አፍራሾች ብለው ይከሳሉ። ቀጥሎም የኤርትራው ድርጅትንና የውጭ ሃይሎችን በጣልቃ ገብነት ፈርጇል። የትግራይ ህዝብ እስካሁን የደማው እንዳይበቃው ከነዚህ “ጠላቶች” የሚልዋቸው ጋር እንዲዋጉላቸው ይቀሰቅሳሉ። መዋሸት ኣመል ሆኖባቸው ነው እንጂ የትግራይ ህዝብ ይህ ነው የሚባል ጠላት የለውም።

ከዚህ አልፎም የህወሓት አመራሮች ባሳዩት አምባገነናዊ፣ ዘራፊና ፀረ-ህዝብ አገዛዝ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ አንቅሮ ሲተፋቸው የዚህን አሉታዊ እሳቤ ሰላማዊውንና ለፍቶ አደሩን የትግራይ ተወላጅ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የነሱን ሐጥያት ገፈት ቀማሽ አድርገውታል። አሁንም የትግራይ ህዝብ “የተከበሃል፣ መጡብህ” አዋጅ ነጋሪት የሚነፉት የትግራይ ህዝብን ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ወገኑ ጋር በማጣላትና በማወናበድ የትግራይ ህዝብን ከጎናቸው በማሰለፍ ስልጣናቸውን ለማቆየት መሆኑን የትግራይ ህዝብ ልብ ሊለውና ከትዴፓ ጋር ተሰልፎ ሊታገለው ይገባል።

በአጠቃላይ አስቸኳይ ጉባኤውን ተከትሎ የወጣው መግለጫ ምንም ምክንያታዊነት የሌለው፣ በውሸት የታጨቀ፣ ለሀገርና ለህዝብ ፋይዳ ቢስ የሆነ የኢትዮጵያ ህዝብን ባጠቃላይ በዋናነት ደግሞ የትግራይ ህዝብን ላለፉት 27 ዓመታት መቀመቅ የከተቱት የህወሓት ጥቂት አመራሮች የስልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ እና የትግራይ ህዝብን መከራና ጭቆና ማስቀጠያ መሆኑን በጥብቅ እየተቃውምነው፤ የትግራይ ብሎም የኢትዮጵያ ህዝቦችም ይኸንን የኣምባገነኖች መግለጫ ውድቅ በማድረግ እንዲኮንኑት በፅናት እንጠይቃለን።

**ድል ለሰፊው ሕዝባችን!!**

**የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ**

**30 ታሕሳስ፣ 2012 ዓ/ም**

**ስልክ ቁጥር +251-118-65-13-36/+251-914-73-35-39/+251-940-79-08-22**
**Website: tigraydemocraticparty.com, email:tigraydemocraticparty@gmail.com**
**የካ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 13፣ ኣያት ጌት ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቤ.ቁ. 519፣ አዲስ አበባ፣**
**ገብረየሱስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቤ.ቁ. 59፣ መቐለ**

ስልክ ቁጥር +251-118-65-13-36/+251-914-73-35-39/+251-940-79-08-22
Website: tigraydemocraticparty.com, email:tigraydemocraticparty@gmail.com
የካ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 13፣ ኣያት ጌት ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቤ.ቁ. 519፣ አዲስ አበባ፣
ገብረየሱስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቤ.ቁ. 59፣ መቐለ